ጽአደራ ፖሊሲ- ጥር 26, 2021

## I. ዓላማ

አንድ ፌየርፋክስ (One Fairfax) የካውንቲው የጎሳ፣ ዘር እና የቋንቋ ብዝሀነት የካውንቲው ጥንካሬ ዋነኛ ምንጭ እንደሆነ ይቀበላል። ካውንቲው የስደተኝነት ወይም የዜግነት ደረጃቸው ምንም ይሁን ምን የሁሉንም ነዋሪዎች መብቶች ለማስከበር እና በጠንካራ ኢኮኖሚያችን ውስጥ እኩል የመሳተፍ እድል ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ይተጋል። የህዝብ አደራና ሚስጥር መጠበቅ ፖሊሲ (የአደራ ፖሊሲ) የወጣው ስደተኛ ነዋሪዎች የሚሰጡት መረጃ ለፌደራል የኢሚግሬሽን ባለስልጣናት ይገለጻል ብለው ሳይሰጉ የካውንቲውን ጥቅማ ጥቅሞችና አገልግሎቶች ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ በማረጋገጥ የአሁኑን የካውንቲውን ፖሊሲ እንደገና ለማረጋገጥ፣ የማህበረሰቡን ጤና፣ ደህንነት፣ ምቾትና ዋስትና ለማሻሻል እና መተማመንን ለመገንባት ነው። ፖሊሲው የፌደራል የኢሚግሬሽን ህግን መፈጸምን ለማመቻቸት የፌየርፋክስ ምንጮች ያለ አግባብ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረጊያ አይደለም፣ ህጉን ማስፈጸም የፌደራሉ መንግስት ብቸኛ ኃላፊነት ነው። ከሲቪል አስተዳደራዊ የኢሚግሬሽን አስፈጻሚ ጋር የሚደረግ ትብብር በተለይም የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ሕገ መንግስታዊ ጥበቃዎች የሚጎድሉት በመሆኑ እና የICE የሲቪል እስር ጥያቄዎች በተደጋጋሚ በስህተት የሚሰጡ በመሆኑ ምክንያት ችግር የሚፈጥር ነው። ካውንቲው ሁሉንም ከኢሚግሬሽንና የጉምሩክ አስፈጻሚ (ICE) እና ሌሎች የፌደራል የኢሚግሬሽን ባለስልጣናት እንዲሁም ህጋዊ የፍርድ ቤት ትእዛዞችና የፍርድ ቤት መጥሪያ ጋር መተባበርን የሚያዙ የፌደራልና የግዛት ህግ እና ደንቦች የሚያከብር ቢሆንም ለተጨማሪ የኢሚግሬሽን የማስፈጸም ጥረቶች ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል የግል ማንነትን የሚያሳውቅ መረጃን መግለጽን ይከለክላል።

## II. ፍቺዎች/ ትርጉሞች

**አስተዳደራዊ ማዘዣ**: ከተጠረጠሩ የኢሚግሬሽን ህግ ጥሰቶች ጋር በተያያዘ የዩናይትድ ስቴትስ የሀገር ውስጥ ደህንነት መምሪያን (DHS)፣ የዩናይትድ ስቴትስ የኢሚግሬሽንና የጉምሩክ አስፈጻሚን (ICE) ወይም አስተዳደራዊ የኢሚግሬሽን ዳኛን (IJ) ጨምሮ በኢሚግሬሽን አስፈጻሚ ባለስልጣን የሚወጣ ሰነድ ነው። ቃሉ የሲቪል አስተዳደራዊ ማዘዣዎችን፣ አስተዳደራዊ መጥሪያዎችን፣ የእስር መጠየቂያዎችን፣ የማስወጫ ትእዛዞችን፣ የዳታቤዝ ምዝገባዎችን (ምሳ፡ ከብሔራዊ የወንጀል መረጃ ማዕከል የሚሰጡ) እና ማንኛውንም ተመሳሳይ የግለሰብ እስር ወይም የመረጃ መስጠት የሲቪል ትእዛዝን ያጠቃልላል። አስተዳደራዊ ማዘዣ የወንጀል ፍርድ ማዘዣ አይደለም።

***መምሪያ***: ሁሉም የፌየርፋክስ ካውንቲ የመንግስት ድርጅቶች፣ መምሪያዎች እና ሌሎች ካውንቲውን ወክለው እንዲሰሩ የተፈቀደላቸው የካውንቲ ሰራተኞች ናቸው።

**የዜግነት ወይም የኢሚግሬሽን ደረጃ**: ዜግነት አንድ ሰው የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ መሆን አለመሆኑን (ከሌላ አገር ዜግነት በተጨማሪ የዩናይትድ ስቴትስ ዜግነት ያዥ ግለሰቦችን ጨምሮ) ወይም ሙሉ በሙሉ የሌላ አገር ዜጋ መሆን አለመሆኑን ("ዜጋ ያልሆነ") የሚገልጽ ነው። የኢሚግሬሽን/ስደተኝነት ደረጃ ዜጋ ያልሆነ ሰው ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ለመገኘት ያገኘውን ፍቃድ አይነት (ምሳ፡ ህጋዊ ቋሚ ነዋሪነት፣ በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ቋሚ ነዋሪነት፣ ቪዛ ያዥነት፣ ጊዜያዊ ጥበቃ የማግኘት ደረጃ ወይም አለመመዝገብ እና ሌሎችንም የደረጃ አይነቶች) ይገልጻል። የታወቀ ዜግነት ወይም የኢሚግሬሽን ደረጃ አንድ ሰው ዜጋ አለመሆኑን ወይም ያልተረጋጠ የስደተኝነት ደረጃ ያለው መሆኑን የሚጠቁሙ ባህሪያትን ይገልጻል፤ ለምሳሌ ትክክለኛ ወይም የሚገመት የትውልድ ቦታ፣ የትውልድ አገር፣ የዘር ሀረግ፣ የትውልድ ቋንቋ፣ "የውጭ አገር ተወላጅ" መመሰል ወይም ይህን ማመላከት፣ እና ማንኛውም ሌላ የብሔራዊ ማንነት ጠቋሚ ወይም የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር አለመኖር። እነዚህ ባህሪያት "ከዜግነት ወይም የስደተኝነት ደረጃ" የተለዩ እና በዚህ ውስጥ የማይካተቱ ናቸው።

**የግል ማንነት መለያ መረጃ**: ማንኛውም ለየብቻም ሆነ ከሌሎች የግል ወይም ማንነትን ለይተው ከሚያሳውቁ መረጃዎች ጋር ሲጣመር የአንድን ግለሰብ ዜግነት፣ የስደተኝነት ደረጃ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ ዘር፣ ጎሳ፣ የቋንቋ ችሎታ፣ ሀይማኖት፣ የጾታ መገለጫ፣ የጾታ ማንነት፣ አካል ጉዳተኝነት፣ እድሜ፣ የትውልድ ቦታና ቀን፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የቤት ውስጥ ጥቃት ወይም የዘማችነት ደረጃ፣ እና የመንግስት መለያዎች ደረጃ (የመንጃ ፍቃድ፣ እንደ የጣት አሻራና የፊት መገለጫ የመሳሰሉ የአሻራ መረጃ፣ የማህበራዊ ዋስትና/የግብር ከፋይ መለያ/ፓስፖርት/የቪዛ ቁጥሮች)፣ የመንግስት ድጎማ/አገልግሎቶች ማግኘት፣ የመኖሪያ ቤት መዝገቦች ወይም የግብር መዝገቦች ለይቶ ለማወቅ ወይም ለመከታተል ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል መረጃ ነው።

ቃሉ በተጨማሪም መኖሪያ ቤት/የስራ ቦታ አድራሻን፣ ግለሰብን ማግኛ ዘዴን እና እንደ ከእስር መልቀቂያ ዳታ ያሉ የህግ ማስፈጸም መረጃዎችን ጨምሮ በእነዚህ ላይ ብቻ ሳይወሰን ዜጋ ያልሆነን ወይም ያልተረጋገጠ የስደተኝነት ደረጃ ያለውን ሰው ለይቶ ለማወቅ፣ ለማነጋገር እና/ወይም ያለበትን ለማግኘት ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል መረጃን ያጠቃልላል።

**የፍርድ ቤት ትእዛዝ**: አስተዳደራዊ የኢሚግሬሽን/ስደተኞች ፍርድ ቤትን ሳይጨምር በግዛት ወይም የፌደራል ፍርድ ቤት የሚሰጥ ትእዛዝ ነው።

**የወንጀል የፍርድ ቤት ማዘዣ**: የፌደራል፣ የግዛት ወይም የአካባቢ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ጥሰት ተፈጽሟል ብሎ ለማመን የሚያበቃ አሳማኝ ምክንያት ሲገኝ በግዛት ወይም የፌደራል ፍርድ ቤት የሚሰጥ ማዘዣ ነው።

**ሰራተኛ**: እዚህ ላይ የካውንቲው ሰራተኛ፣ ወኪል ወይም ተወካይ ተብሎ በሚገለጸው መሰረት ማንኛውም በካውንቲው የተቀጠረ ወይም ካውንቲውን ወክሎ የሚሰራ ሰው ነው።

**የቤተሰብ አባል**: የአንድ ሰው (1) የቅርብ ቤተሰብ ወይም ዘመድ፣ (2) የቤት ውስጥ አኗኗሪ ወይም የአኗኗሪው የቅርብ ቤተሰብ ወይም ዘመድ፣ (3) የማደጎ ወላጅ ወይም ልጅ ወይም የማደጎ ወላጅ/ልጅ የቅርብ ቤተሰብ ወይም ዘመድ፣ (4) በፍርድ ቤት የተሾመ ህጋዊ ጠባቂ አሳዳጊ ወይም የግለሰቡ አሳዳጊ ወይም (5) ወይም ከግለሰቡ ጋር በመደበኛነት በተመሳሳይ ቦታ አብሮ የሚኖር ሰው ነው።

**የኢሚግሬሽንና ጉምሩክ አስፈጻሚ (ICE)**: በዩናይትድ ስቴትስ የአገር ውስጥ ደህንነት መምሪያ (DHS) ስር የሚሰራ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የኢሚግሬሽን ህጎችን የማስፈጸም እና በዩናይትድ ስቴትስ አስተዳደራዊ የኢሚግሬሽን ክርክሮች ላይ የመቅረብ ኃላፊነት የተሰጠው የፌደራሉ የህግ አስፈጻሚ ድርጅት ነው። ይህ ፍቺ በተጨማሪም ማንኛውንም የICE ተከታይ ድርጅትን ያጠቃልላል።

**የኢሚግሬሽን አስፈጻሚ ባለስልጣን**: የICE፣ DHS እና የዩናይትድ ስቴትስ የፍትህ መምሪያ (DOJ) ወኪሎችን ጨምሮ በእነዚህ ላይ ብቻ ሳይወሰን ማንኛውም በኢሚግሬሽን የማስፈጸም ስራዎች ላይ የሚሳተፍ የፌደራል ሰራተኛ ወይም ወኪል ነው።

## III. ሚስጥር መጠበቂያ እና የህዝብ አደራን ማሻሻያ ደረጃዎች

A. <u>*መረጃ መጠየቅ፣ ማግኘት ወይም መግለጽ የተከለከለ መሆን*</u>

1. *የዜግነት ወይም ስደተኝነት ደረጃ።* ማንኛውም ሰራተኛ መረጃ መስጠቱ (ሀ) በህጋዊ የግዛት ወይም የፌደራል ህግ ወይም ደንብ፣ የዳኛ ማዘዣ ወይም የፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም የፍርድ ቤት መጥሪያ ካልተጠየቀ ወይም “[የትኛውም] ሌላ የፌደራል፣ የግዛት ወይም የአካባቢ ህግ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የፌደራል፣ የግዛት ወይም የአካባቢ አስተዳደር ተቋም ወይም ባለስልጣን የትኛውንም ሌላ የመንግስት ተቋም ወይም ባለስልጣን የየትኛውንም ግለሰብ ዜግነት ወይም የስደተኝነት ደረጃ፣ ህጋዊነት ወይም ህገወጥነት የተመለከተ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት መረጃን እንዳይሰጥ መከልከል ወይም በማናቸውም መልኩ መገደብ የለበትም።” በማለት የሚደነግገውን 8 U.S.C. § 1373(a)ን ለማሟላት ካልሆነ በስተቀር ወይም (ለ) በግለሰቡ ወይም በአሳዳጊው ካልተፈቀደ በስተቀር የካውንቲውን መዝገቦች መጠየቅ፣ መመዝገብ/መቅዳት፣ ማግኘት ወይም የአንድን ግለሰብ የዜግነት ወይም የስደተኝነት ደረጃ ለማንኛውም ሰው ወይም ተቋም መግለገጽ የለበትም። በዚህ የአደራ ፖሊሲ ስር የተካተተ ማንኛውም ነገር ከፌደራሉ ህግ ጋር እንደሚቃረን ተደርጎ መወሰድ የለበትም።

2. *ሌላ የማንነት መለያ መረጃ*፡ ማንኛውም ሰራተኛ መረጃ መስጠቱ (ሀ) በህጋዊ የግዛት ወይም የፌደራል ፍርድ ቤት ህግ ወይም ደንብ፣ የዳኛ ማዘዣ ወይም የፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም የፍርድ ቤት መጥሪያ ካልተጠየቀ በስተቀር፣ (ለ) በግለሰቡ ወይም በአሳዳጊው ካልተፈቀደ በስተቀር፣ ወይም (ሐ) የፌየርፋክስ መምሪያን ተልዕኮ ወይም ግዴታዎች ለማሟላት አስፈላጊ ካልሆነ እና መግለጹ የተቀባዩን ተልእኮ ወይም ግዴታ ለማሟላት በሚያስፈልገው ልክ ካልተገደበ በስተቀር የካውንቲውን መዝገቦች/ዳታቤዝ መጠየቅ፣ መመዝገብ/መቅዳት፣ ማግኘት ወይም ማንኛውንም የማንነት መለያ መረጃ ለማንኛውም ሰው ወይም ተቋም መግለገጽ የለበትም።

   የአስፈላጊነት ውሳኔው በድርጅቱ መመሪያዎች መሰረት እና በተቆጣጣሪው አካል ፍቃድ ብቻ መወሰን አለበት።

3. *ሀግ ማስፈጸም*፡ ጠቅላላ ትእዛዞች (ጠቅላላ ትእዛዝ 604ን፣ የስተኝነት ደረጃን፣ ዜግነትን፣ እና ብሔራዊ ማንነትን ጨምሮ)፣ መደበኛ የአሰራር ሥነ ሥርዓቶች (SOPs)፣ እና ሌሎች የፌየርፋክስ ካውንቲ ፖሊስ መምሪያን (FCPD) የሲቪል የኢሚግሬሽን ህጎችና ህገ ደንቦችን ባለማስፈጸም፣ ወይም በአስተዳደራዊ የኢሚግሬሽን ማዘዣዎች መስጠት፣ የFCPD ፖሊሲና ሥነ ሥርዓት ቁጥጥር ላይ ባለመሳተፍ የማህበረሰብ አደራን የመጠበቅና የማመቻቸት ኃላፊነት የሚያረጋግጡ ወይም እንደገና የሚገልጹ የውስጥ ፖሊሲዎች። በተለይም ጠቅላላ ትእዛዝ 604 ይህን ፖሊሲ እንደሚያሟላ ታውቋል። እንዲሌሎች የካውንቲው ድርጅቶች ሁሉ የFCPD ፖሊሲዎች የአደራ ፖሊሲ ከላይ በA1 እና A2 ስር በተገለጹት ደረጃዎች መሰረት የአደራ ፖሊሲውን ስለማክበራቸው ለማረጋገጥ ይገመገማሉ።

4. *ልዩ ሁኔታዎች*፡ (ሀ) *ጥበቃዎች ወይም ጥቅማ ጥቅሞች:* የአንድ ግለሰብ የዜግነት ወይም ስደተኝነት ደረጃ በግዛት ወይም የፌደራል ህግ ወይም ደንብ ስር ለግለሰቡ ጥበቃዎችን ወይም ጥቅማ ጥቅሞችን የሚያስገ ከሆነ ወይም ይህ በአለም አቀፍ ስምምነት የሚጠየቅ ከሆነ የድርጅት ሰራተኛ ለግለሰቡ ስለተገቢው ጥበቃ ወይም መስፈርት በማሳወቅ ለግለሰቡ በፍቃደኝነት ስለ ዜግነት ወይም የስደተኝነት ደረጃው የሚገልጽበት እድል ሊሰጠው ይችላል። (ለ) *ለፕሮግራም ግምገማ የሚውል የሥነ ህዝብ መረጃ:* በዚህ ክፍል ስር የተካተተ ማንኛውም ነገር ዳታው በሚስጥር እስከተያዘና ከካውንቲው ውጭ እስካልተገለጸ ድረስ ከዜግነትና የስደተኝነት ደረጃ ውጭ ለፕሮግራም ግምገማ ጠቃሚ የሆነ (ምሳ፡ የአለመመጣጠን ጥናት) መረጃን መሰብሰብና ማሳተምን አይከለክልም። እዚህ ላይ የተካተተ ማንኛውም ነገር ማንነትን እንዳይገልጽ ተደርጎ የተጠቃለለ መረጃን ከካውንቲው ውጭ መግለጽን እንደሚገድብ ተደርጎ መወሰድ የለበትም።

B. <u>የመንግስት አገልግሎቶችና ምንጮችን ማግኘት መከልከል</u>

ሰራተኞች መረጃው ወይም ግለሰቦቹ እንደሚፈለጉ በሚገልጽ የፌደራል ወይም የግዛት ህግ ወይም ደንብ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ዳኝነት ማዘዣ፣ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም የፍርድ ቤት መጥሪያ ካልታዘዘ በስተቀር ማንኛውንም የካውንቲውን አገልግሎቶች፣ በየትኛውም አገልግሎት ዙሪያ የሚገኝ ንብረትን፣ መሳሪያ፣ መዝገቦች ወይም ዳታቤዞች ወይም ለህዝብ ይፋ ያልሆኑ ፈንዶችን ማግኘትን መፍቀድ የለባቸውም።

C. <u>የካውንቲውን ገንዘቦች ለሲቪል የኢሚግሬሽን ማስፈጸሚያ መጠቀም ስለመከልከሉ</u>

ሰራተኞች የካውንቲውን ሀብቶች (አገልግሎቶችን፣ መሳሪያዎችን፣ ሞባይል ስልኮችን፣ የቢሮ አቅርቦቶችን፣ ራዲዮዎች፣ ኢሜይሎች፣ ዳታቤዞች እና የስራ ሰዓት የሰራተኛ ጊዜን ጨምሮ) የሰራተኛው ድርጊት በዚህ የአደራ ፖሊሲ ስር በግልጽ የሚፈቀድ ካልሆነ በስተቀር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ማንኛውንም የግል ማንነትን ለይቶ የሚያሳውቅ መረጃን ለኢሚግሬሽን አስፈጻሚ ባለስልጣናት ለመስጠት መጠቀም የለባቸውም።

D. <u>ስምምነቶች ወይም ዜግነት ወይም የስደተኝነት ደረጃን መሰረት አድርጎ ቅድመ ሁኔታ የማስቀመጥ ድርጊት ስለመከልከሉ</u>

ሰራተኞች ማንኛውንም ሰው የታወቀ ወይም የታመነ የዜግነት ወይም የስደተኝነት ደረጃውን መሰረት አድርገው፣ ወይም የግለሰቡን የቤተሰብ አባል የታወቀ ወይም የታመነ የዜግነት ወይም የስደተኝነት ደረጃ መሰረት አድርገው ማስፈራራት፣ ማስገደድ ወይም ማዋከብ የለባቸውም። ሰራተኞች በግዛት ወይም የፌደራል ህግ ወይም ደንብ ወይም የፍርድ ቤት ትእዛዝ ካልታዘዘ በስተቀር የካውንቲውን ጥቅማ ጥቅሞች፣ እድሎች ወይም አገልግሎቶች ለማቅረብ የታወቀ ወይም የታመነ የዜግነት ወይም የስደተኝነት ደረጃን በቅድመ ሁኔታነት ማስቀመጥ የለባቸውም።

E. <u>ሲቪል ኢሚግሬሽን ማስፈፀምን ማመቻቸት ስለመከልከሉ</u>

ሰራተኞች በመምሪያው የህግ ካውንስል ከካውንቲው ዋና ጠበቃ ጋር በሚደረግ ምክክር ህጋዊ በሚታመንበት ህጋዊ የግዛት ወይም የፌደራል ህግ፣ የወንጀለኛ መቅጫ የዳኝነት ማዘዣ፣ መሆኑ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም የፍርድ ቤት መጥሪያ ካልታዘዘ በስተቀር በሲቪል የኢሚግሬሽን ማስፈጸም ስራዎች ላይ መሳተፍም ይሁን እነዚህን ማመቻቸት የለባቸውም።

F. <u>በፌደራል ምዝገባዎች ላይ መሳተፍ ስለመከልከሉ</u>

የትኛውም የካውንቲው ሀብቶች ማንኛውንም ግለሰቦችን ዜግነታቸውን፣ የስደተኝነት ደረጃቸውን፣ ዘራቸውን፣ ብሔራዊ ወይም የጎሳ ማንነታቸውን፣ የቋንቋ ችሎታቸውን፣ ጾታቸውን፣ የጾታ ማንነታቸውን፣ የጾታ መገለጫቸውን፣ ሀይማኖታቸውን፣ አካል ጉዳታቸውን ወይም እድሜያቸውን መሰረት በማድረግ መመዝገብን የሚጠይቅ የፌደራል ፕሮግራም ምርመራን ወይም ማስፈጸምን ለማገዝ ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም።

## IV. ተቀባይነት ያላቸው የማንነት መታወቂያ ሰነዶች

A. የካውንቲውን አገልግሎቶች ወይም ጥቅማ ጥቅሞች ለማቅረብ በፌደራል ወይም የግዛት ህግ ወይም ደንብ ወይም ግልጽ የገንዘብ ድጋፍ መስፈርት ካልተጠየቀ በስተቀር ሰራተኞች ከዚህ በታች የተገለጹትን ጨምሮ በእነዚህ ላይ ብቻ ሳይወሰን የአንድን ግለሰብ መኖሪያ ወይም አድራሻ በአሳማኝ ሁኔታ የሚያረጋግጡ ጥምር የማንነት መለያና የአድራሻ ሰነዶች ወይም ሌሎች መረጃዎች መቀበል አለባቸው፡

1. በግዛት እና/ወይም የውጭ አገር መንግስት (ለምሳሌ፡ መንጃ ፍቃድ፣ ፓስፖርት ወይም የቆንስላ መታወቂያ ሰነዶች) ወይም በቅድሚያ ፍቃድ በተሰጠው ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት የተሰጠ ፎቶ የተለጠፈበት መታወቂያ (አይዲ)።
2. የአይዲ ምትክ የሆነ ቅጽ ማቅረብ ግለሰቡን ለከፍተኛ ደረጃ ምርመራ ወይም ግለሰቡ መንጃ ፍቃድ ወይም የግዛት መታወቂያ ካርድ ቢያቀርብ ያገኝ ከነበረው ለተለየ አያያዝ ማጋለጥ የለበትም።

B. ይህ ክፍል የፌደራል I-9 ቅጾችን ወይም በተገለጹ ሁኔታዎች ስር ልዩ የመታወቂያ ወይም ፍቃድ ቅጾችን የሚጠይቁ ተመሳሳይ የግዛት ቅጾችን በመሙላት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

## V. ኃላፊነቶች

A. <u>ሰራተኞች</u>

1. በካውንቲው የሰራተኞች ደንቦች ምዕራፍ 16 መሰረት ሁሉም የግል ማንነት መለያ መረጃ በጥብቅ ሚስጥርነት መያዝ አለባቸው።
2. በአደራ ፖሊሲው ስር የተገለጹት ደረጃዎች መከበር አለባቸው።
3. የመምሪያ ኃላፊዎች ሁሉንም ከመምሪያው የሚደርሷቸውን ከአደራ ፖሊሲ ጋር ተያያዥ አስተዳደራዊ ወይም የዳኝነት ማዘዣዎች ፖሊሲውን ማክበር አለማክበራቸውን ለመወሰን ለካውንቲው የዋና ጠበቃ ቢሮ መምራት አለባቸው።
4. አንድ ድርጊት በህጋዊ የግዛት ወይም የፌደራል ህግ ወይም ደንብ የሚጠየቅ መሆኑን፣ የፌየርፋክስ ካውንቲ መምሪያን ተልእኮ ወይም ግዴታዎች ለማሟላት አስፈላጊ መሆኑን እና/ወይም በአግባቡ በዚህ ይዘት አድማስ ልክ የተገደበ መሆኑን ለመወሰን በመምሪያዎቻቸውና ካውንቲው የተደነገጉ መመሪያዎችን ማክበር አለባቸው። መመሪያዎቹ የጥያቄውን አይነት፣ ማግኘት ወይም መግለጽ በግልጽ ካልፈቀዱ በስተቀር ሰራተኞች የትኛውንም የግል ማንነት መለያ መረጃ ማግኘትን ከመፍቀዳቸው በፊት የመምሪያ ኃላፊያቸውን ፍቃድ ማግኘት አለባቸው።
5. አንድን ግለሰብ ለማሰር ወይም የግለሰቡን መረጃ ለመስጠት አስተዳደራዊ ማዘዣ፣ የፍርድ ቤት ትእዛዝ፣ የፍርድ ቤት መጥሪያ ወይም ሌላ የሲቪል ኢሚግሬሽን ጥያቄ በደረሰ በ48 ሰዓት ውስጥ ስለጥያቄው ፍሬ ጉዳይ ማማከር/መጠየቅ አለባቸው። ጥያቄው የቀረበው በጽሁፍ ከሆነ የጥያቄው ፍሬ ጉዳይ በጥያቄው ኮፒ ተደግፎ መቅረብ አለበት።

B. <u>የካውንቲው ጠበቃ ቢሮ</u>

1. የመምሪያ ኃላፊዎች ለየትኛውም የህግ ጥያቄዎች በዚህ አደራ ፖሊሲ ስር የተጤቀው መረጃ መሰጠት ያለበት ስለመሆኑ አስመልክተው የካውንቲውን ጠበቃ ቢሮ ማነጋገር አለባቸው።

2. በመምሪያ ኃላፊ ሲጠየቅ የካውንቲው የጠበቃ ቢሮ የሚፈለገውን መረጃ ወይም ግለሰብ በተመለከተ የፌደራል ወይም የግዛት ህግ ወይም ደንብን፣ የወንጀለኛ መቅጫ የዳኝነት ማዘዣ፣ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም የፍርድ ቤት መጥሪያን ለማሟላት ካውንቲው የተጠየቀውን ጥያቄ ማሟላቱ በዚህ የአደራ ፖሊሲ ስር አስገዳጅ ስለመሆኑ መወሰን አለበት። በደንብ መሰረት የሚገለጽ መረጃ የካውንቲው የጠበቃ ቢሮ ደንቡ የወጣው በአውጪው የስልጣን አድማስ ስልጣን ልክ መሆኑን ከወሰነ ብቻ መገለጽ አለበት። በዳኝነት ማዘዣ፣ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም የፍርድ ቤት መጥሪያ መሰረት የሚገለጽ መረጃ መግለጹን በሚያዘው ሰነድ ይዘት አድማስና መስፈርቶች ልክ የተገደበ መሆን አለበት። ይህ ካልሆነ ካውንቲው ጥያቄውን ለመሰረዝ ወይም መረጃውን ለመጠበቅ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ ክርክሮችን ይመሰርታል።

3. አስፈላጊውን መረጃ ለመስጠት ከመምሪያው ጋር አብሮ መስራት አለበት።

C. <u>የመምሪያ ኃላፊዎችና ሥራ አስኪያጆች</u>

1. በክፍል III መሰረት መሰብሰብ ወይም መገለጽ ያለባቸውን ወይም የሌለባቸውን የሚስጥር መረጃ አይነቶች የሚገልጹ መመሪያዎችን ለማካተት የዚህን ሥነ ሥርዓት እና ፖሊሲ መምሪያ አቀፍ ትግበራና መከበር ማረጋገጥ አለባቸው። መመሪያዎቹ በፌየርፋክስ ካውንቲ ድረገጽ ላይ ታትመው መውጣት አለባቸው።

2. ለዚህ ፖሊሲ ጥሰቶች በካውንቲው የሰራተኞች ደንቦች ምዕራፍ 16 ወይም ሌሎች የሥነ ምግባር ሥነ ሥርዓቶች ተገቢ ሆኖ በሚገኘው መሰረት ለፖሊሲው ጥሰቶች ተገቢ የሥነ ምግባር እርምጃዎችን በመውሰድ መፍትሄ መስጠት አለባቸው።

3. የዚህን የአደራ ፖሊሲ የሚስጥር መጠበቅ መስፈርቶች ለማክበር የህግ ማስፈጸም አገልግሎቶችና እርምጃዎችን ጨምሮ ከፈየየርፋክስ ካውንቲ ጥቅማ ጥቅሞች፣ እድሎች ወይም አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሁሉንም ቅጾች መገምገም አለባቸው። ፖሊሲው ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በ120 ቀናት ውስጥ (ሀ) በግዛት ወይም የፌደራል ህግ ከሚጠየቁት ውጭ ማንኛውም ዜግነትን፣ የስደተኝነት ደረጃን ወይም የትውልድ አገርን የተመለከቱ ጥያቄዎች መሰረዝ አለባቸው እንዲሁም (ለ) ሌላ የሚስጥር የግል መረጃን የተመለከቱ ጥያቄዎች መሰረዝ ወይም ይህን ፖሊሲ ባከበረ መልኩ መሻሻል አለባቸው።

4. የአሁንም ሆነ የወደፊት የግል መረጃን መገለጽን እና በዚህ የአደራ ፖሊሲ ስር ምን መረጃ መገለጽ እንዳለበት የሚጠይቁ እርዳታዎችና ውሎችን እንዲሁም ከግል አገናኞች ጋር የሚፈጸሙ ውሎችን መቆጣጠር አለባቸው።

5. ይህ የአደራ ፖሊሲ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ የመምሪያ ኃላፊዎችና ስራ አስኪያጆች የመመሪያው ሰራተኞች የዚህን የአደራ ፖሊሲ ድንጋጌዎች ማክበራቸውን ለማረጋገጥ ግምገማ ያካሂዳሉ።

D. <u>የካውንቲው ስራ አስፈጻሚ</u>

1. የካውንቲው ስራ አስፈጻሚ ከላይ በV C 3 እና 4 ስር የመምሪያውን እርምጃዎች ይገመግማል እንዲሁም ይህ የአደራ ፖሊሲ መከበሩን ለተቆጣጣሪዎች ቦርድ ያረጋግጣል።

2. በክፍል IV ስር አይዲዎቻቸው ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ቡድኖች ፍቃድ የሚያገኙበትን ሥነ ሥርዓት በአግባቡ ያዘጋጃል እንዲሁም የተፈቀዱ አይዲዎችን በካውንቲው ድረገጽ ላይ ይዘረዝራል።

## VI. *ተነጣጣይነት*

*የዚህ ፖሊሲ ድንጋጌዎች ተነጣጣይ ናቸው። የዚህ ፖሊሲ የትኛውም ክፍል፣ ድንጋጌ ወይም ዙር ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ህጋዊነቱን ካጣ የዚህ ህጋዊነት ማጣት በቀሪዎቹ ክፍሎች፣ ድንጋጌዎችና ዙሮች ተፈጻሚነት ላይ ተጽእኖ አይፈጥርም። ካውንቲው ይህ ህጋዊነቱን ያጣ ክፍል፣ ድንጋጌ ወይም ዙር ሳይካተት ይህን ፖሊሲ ስለማጽደቅ ያቅዳል።*